**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

*Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity*

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፐሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band*


***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***መጋቢት 23 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

## ለዓባይ መቀራመት ፤ ኢትዮጵያን ማጥፋት

## የሱዳንና የግብፅ መሪዎች ፤ በካርቱም ከወያኔ ጋር የተፈራረሙት ውል

## ኢትዮጵያን የሚጎዳ ሰነድ ነው

በመጋቢት 14 ቀን 2007 ዓም ( ማርች 23 2015) በሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ላይ፤ የግብጽና የሱዳን መሪዎች ተገናኝተው በዐባይ ወንዝ ኣጠቃቀም ዙሪያ ከወያኔ ወኪሎች ጋር አንድ ስምምነት እንደተፈራረሙ ተገልጿል ። የስምምነቱንም ሰነድ ይፋ አድርገዋል። ግብጾችና ሱዳኖች ለየሀገሮቻቸው የሚጠቅም ውል ተፈራርመው መሄዳቸው የሚያስገርም አልነበረም ። የዚህን ስምምነት ወሬ የሰሙ የተለያዩ የዜና አውታሮች በሰፊው አስተጋብተውታል ። ቢቢሲና ኢ.ኤፍ. ፒ. ሰፊ ሽፋን ሰጥተውት ነበር ። ኢየሩሳሌም ፖስት የተሰኘው የእስራዔል ዕለታዊ ጋዜጣ እንደ ሰበር/ትኩስ/- ዜና ደርጃ አቅርቦ፤ በሰፊው አትቶበታል ። አል አህራም የተሰኘው የግብፅ ዕለታዊ ዐረብኛ ጋዜጣም በበኩሉ ሰነዱን በተለያዩ ቋንቋዎች ትርጉሞ አሳትሞ አሰራጭቶታል ። አል አህራም ጋዜጣ በሰነዱ ላይ ላሜ ወለደች ብሏል። ሁሉም ይህንን ማድረጋቸው ፤ የየራሳቸው ምክንያቶች ስለአሏቸው ነው ።

በዓለም አቀፍ የውሃ አጠቃቀም ጥናትና ምርምር ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ፤ ይህ ስምምነት በኢትዮጵያ ላይ የሚያስከትለውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ በዝርዝር እንደሚተቹበት ይጠበቃል ። የስምምነቱን ሁለንተናዊ ገፅታ ማወቅ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ መብቱ ስለሚሆን፤ በሙያው የሠለጠኑ ምሁራን ግዴታቸውን እንደሚወጡ ተስፋ ይደረጋል ። እስካሁን ድረስ ፤ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ተገቢውን ትንተና ሰጥተዋል ። አበጃችሁ ሊባሉም ይገባል !

የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ መንግሥት በአሁኑ ወቅት ባለመኖሩ፤ ይህን የካርቱም ስምምምነት የፈረሙ ሱዳንና ግብፅ፤ የፈለጉትን እንዳገኙ መጠርጠር አይቻልም ። ይህም በሰፊው

እየተነገረ ይገኛል ። ኢትዮጵያ፤ የራሷ አንጡራ ሀብት የሆነውን ዐባይን ( ግዮንን ) እንደፈለገችው የመጠቀም መብቷን ለማስከበር፤ የማንንም ፈቃድና ቡራኬ የማትፈልግ ሀገር መሆኗን መታወቅ ነበረበት ። ይህንን መሠረታዊ ሀቅ አለመገንዘብ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንነት አለማወቅ ይሆናል ። ይህ የካርቱሙ ስምምነት ሰነድ በአመዛኙ፤ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የደፈረና ሀገራዊ ጥቅሟንም የተፈታተነ ሆኗል ። ይህ ስምምነት ግብፅን ሦስት ጥቅሞችን ሰጥቷታል ።

1ኛ. በኢትዮጵያ ግድብ እንቅስቃሴ ላይ፤ የይገባኛልና ከባለቤትነት ባላነሰ ሁኔታ ኢትዮጵያን አሳሪ ስምምነት ለመፈራረም ችላለች። በአንድ ሉዓላዊት ሀገር፤ ( ኢትዮጵያ) ውስጥ በተገነባ ግድብ ላይ የግድቡን ሥራ፤ ከኤሌክትሪክ ማመንጨት ባለፈ፤ በምንም ነገር ኢትዮጵያ እንዳትጠቀም ያስገድዳታል ። ይህም ማለት፤ ውሀው በግድቡ ውስጥ ገብቶ የመብራት ማመንጫ ተርባይኑን ከመታ በኋላ መለቀቅ እንዳለበት ያረጋግጥል ። የግድቡን ተግባርና አግልግሎት ወስኖታል። ኢትዮጵያ በግድቡ ውሃ የመስኖ አግልግሎት መጠቀም አትችልም ።ከግድቡ በሚገኘው ውሃ አካባቢውን ለማልማትና የዕርሻ ልማት ማካሄድ አትችልም ። በራሷ ውሃ የራሷን ልማት ማካሄድ እንዳትችል ያደርጋታል ። ይኮደኩዳታል ።

2ኛ. ለግብፅ የሚጠቅም አጠቃላይ ድፍን ቃላትን መጠቀሙ፤ለወደፊት የግብፅ ጠብ መጫሪያነት በቀላሉ ልትጠቀምበትና ፍትሃዊ ጦርነት እንዳደረገች ዐለም አቅፍ ኅብረተሰቡን ለማሳምን የሚረዳት ማጠየቂና ድልዳል አመቻችቶላታል ። ለምሳሌ አንቀፅ ሦስት ( 3 ( PRINCIPLE OF NOT CauSING SIGNIFICANT DAMAGE ) {ፐርንስፐል ኦፍ ኖት ኮዚንግ ሲግኒፊካንት ዳሜጅ } " **በወንዙ አጠቃቀም ላይ ዓይነተኛ አደጋ አለመሆን** በሚለው ስር **አደጋ የሚለው ቃል ምን ማለት እንደሆነ ወይንም የትኛው አደጋ እንደሆነ አያብራራም ። ለግብፅ አደጋ ኢትዮጵያ የግድቡን ውሃ ለመስኖ መጠቀም ይሆናል ። የስምምነቱ አንቀጾች** ግልፅ በሆነ መልኩ አለመቀመጥ፤ ግብፅ በፈለገችው መንገድና በማነኛውም ጊዜ የፈለገችውን ትርጉም የሚሰጣትን ካርታ ለመምዘዝ ያስችላታል ።

3ኛ. ይህ የካርቱም ስምምነት፤ ያለፈውን የግብፅንና የሱዳንን የቅኝ ግዛት ስምምነት ውል አያጣጥለውም ። ከዚህ በፊት የቅኝ ግዛቱን ውል ኢትዮጵያ የማትቀበለው መሆኑን በተደጋጋሚ አጋጣሚዎች ገልጻለች ። በዚህ በአሁኑ ስምምነት ላይ፤ የቅኝ ግዛቱን ውል ስምምነት የሚተካ ወይንም የሚቀንስ አንዳችም አንቀፅ የለውም ። ይህ በመሆኑ፤ ግብጽ ወደፊት በፈለገች ጊዜ የምትጠቅሰው ውል እንደሚሆን አመልካች ነው ።ይህ ስምመት የወደፊቱን የግብፅን ስትራተጂያዊ ወይም ዘላቂ ዓላማ በስልት ደረጃ ያገለግላታል ። ይህም ማለት፤ በግብፅ በኩል፤ ከልብ የመነጨ ፍላጎት ነው ? ወይስ

ለጊዜያዊ ስልት መጠቅሚያ መደላድል ማስቀመጫ ነው ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት እንገደዳለን ማለት ነው ። ከልብ እናልሆነ ግን እንገዘባለን ።

ያካባቢውን ሁኒታና ፖለቲካዊ በቅርብ የሚከታተሉ፤ ታዛቢዎች የሚጠይቁት አንድ ጥያቄ፤ ለምን አሁን ውሉን ለመፈራረም አስፈለገ ? የሚል ነው። በወያኔ በኩል የራሱ አስገዳጅ ምክንያቶች አሉበት ።

ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ ላይ ያለው ጥላቻና ተቃውሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ወያኔን ስጋት ላይ የጣለው መሆኑ ግልጽ ነው። በተለያዩ ቦታዎች የሚንቀሳቀሱ፤ ተቃዋሚ/ ታጣቂ ኃይሎች፤ ስጋት ላይ እንደጣለው ይታወቃል ። በተለይም በሰሜናዊው የጎንደር አርማጭኾና በጠገዴ-ወልቃይት አካባቢ የሚንቀሳቀሱት ታጣቂዎች የዕለት ተዕለት ተግባራቸው የሰፋና እየጎለበተ መሄዱ የወያኔን መውደቂያ ምልክት ሰጭ ሆኗል ። ታፍኖ የተቀመጠው የህዝብ ምሬትና ቁጣ የሚፈነዳበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አስተያየታቸውን የሚሰጡ ታዛቢዎች በርካታ ናቸው ። ስለዚህ ወያኔ፤ የሕዝቡን የትግል አቅጣጫ ለማስቀየር ያደረገው መሰሪነት እንደሆነ ይገመታል። ከዚህ ቀደም መለስ ዜናዊ ለግብጹ ሙባረክ ተንበርክኮ በአባይ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥቅም ለግብጽ አሳልፎ መስጠቱ የሚረሳ አይደለም ።

ግብጽም፤ የራሷ ምክንያት እንዳላት የሚናገሩ ታዛቢዎች አሉ ። እንደ አንገብጋቢ ምክንያት የሚቆጠረው፤ በመካከለኛው ምሥራቅ የተነሳሳው አሸባሪው እስላማዊ ካሊፌት ኃይል ግብጽን ያሰጋት መሆኑ ነው። ከዚህም በላይ፤ በአለፉት ዓመታት የደቀቀው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ችግር ላይ በመሆኑ፤ የአብደል ፈታህ ሲሲን መንግሥት ከፍተኛ ስጋት ላይ እንደጣለው ይነገራሉ ። በዚህ ምክንያት የሚመጣው ሕዝባዊ ቀውስ ፤ ለአካባቢው ጸጥታ አለመረጋጋት ስጋት ሊሆን ስለሚችል፤ የአባይን ስምምነት አስቀድሞ ማረጋገጥ ይኖርበታል ብለው ያስባሉ። ነገሩ ሲጠቃለል፤ በሁሉም ተፈራራሚዎች በኩል ጊዜያዊ የፖለቲካ ውጥረትን ለማርገብ ካልሆነ በስተቀር ዘለቄታ ስምምነትን ያስፍናል አይባልም ።

ከላይ በተጠቀሱት ሦስት አባይት ምክንያቶች ፤ የካርቱሙ ስምምነት ኢትዮጵያን ጎድቷታል። ግብፅ ግን ቀንቷታል ። ሱዳን በመሃል ሰፋሪነቷ መገልበጫዋን አደላድላለች ከማለት በተቀር፤ ያገኘችውም ሆነ ያጣችው ይህን ያህል ነው ማለት አይቻልም ። ለኢትዮጵያ ከጥቃትና ከጉዳት በስተቀር ያመጣው ጠቀሜታ የለውም ። ከወያኔ ዕርባና ስለማይገኝ፤ ይህ መሆኑ አያስገርምም። በኢትዮጵያም ሕዝብ በኩል፤ ከጥርጠሬ ተአማኒነት የለውም ። ለዚህም ሦስት ምክንያቶች አሉ ።

1ኛ. የውሉ ስምምነት፤ አስቀድሞ ሕዝቡ ሳይወያይበትና ሳይመከርበት፤ በምሥጢር ተይዞ የተፈፀመ በመሆኑ ነው ። ይህንን የመሰለ ታላቅ ብሄራዊ ጉዳይ ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲፈራረሙ፤ ቢያንስ ቢያንስ ሕዝቡ ሊወያይበት በተገባ ነበር። ዴሞክራሲ በትፈነበት ሀገር ይህ ይሆናል ተብሎ ባይጠበቅም ቅሉ ።

2ኛ. ተቃውሚምኃይሉም አሳቡን እንዲገልፅ አልተደረገም። በሀገር ታላላቅ ጉዳይ ዙሪያ፤ የተቀዋሚው ክፍል ሃሳብ ሊካተት በተገባ ነበር ፡፤ ይህ ሳይሆን ቀርቷል ። ዘጠና ዘጠኝ በመቶ 99% የህንድ ፓርቲ አገዛዝ በገነነበት ሀገር፤ የመላው ሕዝብ ድምፅ የታፈነ መሆኑ ቢታወቅም፤ በዚህ ምክንያት፤ የ ዓልም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች ሁሉ፤ ሊያገኙ አይችሉም። አይጠበቅምም ።

3ኛ. እስካሁን ድረስ በወያኔ የተፈፀሙት ይከህደት ስምምነቶች፤ መመዝገባቸው፤ ሕዝቡን ጥርጣሬ ውስጥ ከትቶታል ። እነርሱምየሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ በወያኔና በሻአቢያ መካከል የተደረገው የሎንዶን ስምምነት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳያወቀው፤ ኤርትራውያን ወንድሞቻችንን እንዲገነጠሉ ያደረገ በመሆኑ፤ ሌላው ቢቀር፤ ኢትዮጵያ የአሰብን ወድብ እንድታጣ ማድረጉ፤

ለ/ ከሸብያና ከወያኔ ጦርነት በኋላ አልጀርስ ላይ ወያኔ የፈረመው ስምምነት፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጀርባ በስውር የተካሄደ ደባ በመሆኑ፤ ብቻ ሳይሆን የ ኢትዮያን ጥቅም አሳልፎ የጸጠ በመሆኑ፤ የሕዝቡን ጥርጣሬ አጉልቶታል ።

በነኝህ ዐበይት ምክንያቶች፤ የካርቱሙ ስምምነት፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ።

የዛሬ ስድሳ ዓመት አካባቢ ግብፅ ታላቁን የአስዋን ግድብ በዐባይ ወንዝ ላይ ገድባለች። ግድቡን ለመስራት፤ የቀድሞዋ ሶቬየት ኅብረትን የገንዘብ፤ የቁሳቆስ፤ የቴክኒዮሎጅና የዲፕሎማቲክ ርዳታዎችን አግኝታለች ። የሩሲያ መሃንዲሶችም ከግድቡ ምስረታ እስከ ፍፃሜው ድረስ በግድብ ግንባታ ላይ ሙሉ ተባባሪዎች ነበሩ። በ1970 ዓም ግድቡ ሥራውን ከጀመረበት አንስቶ ፤ የግብፅን ሕዝብ ሁለንተናዊ ህይወት ለውጦታል ። መላው የሀገሪቱ ዜጋ የኤሌክትሪክ መብራት ተጠቃሚ ሆኗል ።

በዚህ ግድብ ምክንያት፤ የግብፅ፤ ቴክኒዮሎጅ እድገት ዳብሯል ። የመጓጓዣ፤ የኢንዱስትሪና የዕርሻ ፈጣን ዕድገቶች የተመዘገቡት በግድቡ ግንባታ ምክንያት ነው። በዐባይ ላይ የመንሸራሸርያና መደሰቻ ጀልባዎች የግብፅን የቱሪዝምን እንዱስትሪ አስፋፍተውታል፡ በአሣ እርባታ የሚታፈሰውን ምርት ማየት

ያስደምማል ። ከአስዋን ግድብ እስከ ሜዴቴራንያን ባኅር ድረስ ያለው 1000 ( ሺ ) ኪሎሜትር ርቅት ምድረበዳ መሬት በአረንጓዴ መልክ ያሸበረቀው፤ በዐባይ ውሃ መሆኑን ማንም አይክደውም ። 90 ሚሊዮን የሚሆነው የግብፅ ሕዝብ ሙሉ ተመጋቢ ነው ፡፤ በግብፅ የኢትዮጵያ መሰል ረሃብ የሚባል ነገር አይታወቅም ። ግብፅ ከእርሻና እንዱስትሪ (አግሮ-ኢንደስትርያል ) የምታገኘውን የምርት ሀብት፤ ለራሷ አልፋ ተርፋ ለውጭ ገበያ ታቀርባለች። መላውን የመካከለኛውን ምሥራቅ ገበያ ያጥለቀለቁት ፤ የግብፅ የኢንዱስትሪና የርሻ ውጤቶችና ዕቃዎች ናቸው። ግብጽ ብዙ ሚሊዮን ዜጎቹዋን ምድረበዳ አልምታ ልታሰፍር ፈላጊ ናትና ከአባይ ውሀ ተጨማሪ ውሀን ፈላጊ ናት ፤ስግብግብ ናት ።እኔ ብቻ ልጠቀም ባይ ።

በአንፃሩ፤ የዓባይ ጌታ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ኑሮ ምን እንደሆነ መዘርዘር " ለቀባሪ አረዱት" ስለሚሆን፤ በዚያ ላይ ማተኮሩ ጉንጭ አልፋ ትረካ ይሆናል ። ምፀቱና እንቆቅልሹ ግን፤ የሀገራችን ሕዝብ ዝንተ-ዓለሙን፤ ከድኅነት፤ ከረሀብ፤ ከበሽታ፤ ከማይምነትና ከኋላ ቀርነት እንዳይላቀቅ የተፈረደበት መሆኑ ነው ። ይኸም አልበቃውም ተብሎ፤ ሁል ጊዜ፤ በጦርነት፤ በሽብርና በጭቆና አገዛዝ እየማቀቀ ይኖራል ። ከዚህ ፍዳ ለመላቀቅ ሀገሩን እየለቀቀ የሚሰደደው ዜጋ መላውን ዓለም አጥለቅልቆታል ። ዐባይን መጠቀም ቀርቶ፤ በሀገሩ ላይ ሠላም አግኝቶ ሊኖር አልቻለም ። የዓለም ሕዝብ መዘባበቻና ተመፅዋች መሆኑ፤ ልዩ ምልክቱ እንዲሆን ተደርጓል ።

የዐባይን ግድብ አስመልክቶ፤ ባላፈው ሳምንት፤ ካርቱም ላይ የተደረገው ውል፤ ከላይ የተገለፀውን የሀገራችንን መከራ የሚያጠነክር እንጅ፤ የሚያሻሻል ሆኖ አልተገኘም ። ወትሮውንም ቢሆን፤ ሱዳኖችና ግብፆች ከወያኔ ጋር ያደረጉት ሴራ፤ የተሻለ ነገር ለኢትዮጵያ ያስገኛል ተብሎ አይጠበቅም ነበር ።

ሠላሳ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ይኸው ወያኔ ፤ ከባዕዳን ጋር በመተባበር በመመሳጠር፤ ሁለት ደባዎችን ፈጽሟል። የመጀመሪያው በ 1981 ዓም ሎንዶን ላይ በባዕዳኑ አስተባባሪነት ከሻዕቢያ ጋር ያደረገው ሀገራዊ ክኅደትና ወንጀል ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ ይህ ካርቱም ላይ ባለፈው ሣምንት የተፈፀምው የሀገራችንን ሉዓላዊንትን የጣሰውንና ብሄራዊ ጥቅሟን አሳልፎ የሰጠው ክኅደት ነው ።

ሁለቱንም ክኅደቶች፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ ያወግዛቸዋል ። ይኮንናቸዋል ። ህጋዊነትም ሆነ ተቀባይነት አይኖራቸውም ። የነፃነት ልዕልናውንም ሆነ፤ ብሄራዊ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ትግሉን ይቀጥላል

። ሀገራዊ ክብሩንና ሉዓላዊነቱን ለማስከበር ደግሞ፤ የማንንም በጎ ፈቃድ አይጠብቅም። የማንንም ትብብር አገኛለሁ ብሎም አይመኝም። አይጠብቅምም።

**" እኔ እዘገዋልሁ ደጄን እንዳመሉ ፤**

**የት ሄደ ቢሏችሁ ክፍቶት ሄደ በሉ ። "**

እያለ በገዛ እጁ የራሱን ቤት ይከለካላል ይጠብቃል፤ ነጻነቱ ያስከብራል እንጅ ፤ **" በራሱ ወጀድ፤ ባዕዳን እየመጡ ሞፈር ሊቆርጡ"** አይችሉም። ከእንግዲህ ወዲህ ! ልብ ያለው ልብ ይበል! ልብ የሌለው ልብ ይግዛ እንላለን !

ዛሬ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያጠብቅ መንግሥትም ሆነ፤ ወኔ ያለው ወይም ቢቆርጥም ብቃቱና ችሎታው ያለው ኃይል አልተገኘም። ዜጎቿም እንዳይተባበሩ ተደርገዋል ። ተከፋፍለው እርስ በርሳቸው በዘር እንዲፈራረጁ እየተደረገ ነው ። ግብፅና ሱዳን ያሻቸውን ለማድረግ መልካም አጋጣሚውን አግኝተዋል ። " **ከሞኝ በራፍ ሞፈር ለመቁረጥ** " ተሳክቶላቸዋል ። ጊዜውና ሁኔታው ተመቻችቶላቸዋል ። " **ጊዜ የሰጠው ቅል ደንጋይ ስለሚሰብር** " የአናብስት ሀገረ የነበረችው ኢትዮጵያ ፤ ዛሬ የጃርቶች መጫወቻ ሆናለች። ግን እንዲህ ሆና አትቀርም ። ዜጎቿ ይገናኛሉ። ይወያያሉ። ይመካከራሉ። ይተባበራሉ። ስሜታዊነት ወደ ምክንያታዊነት ይለወጣል ። ጨለምተኝነት እያከሰመ ፤ብሩኅታዊነት ይስፍናል ። ለሁሉም የጋራ የሆነች ሀገሩን ፤ የሁሉም ዜጋ ተጠቃሚ እንድትሆን ተግቶ ይታገላል ። ይህ ሁሉ ሊሳካ የሚችለው ግን መሠረታዊ ለውጥ ሲኖር ነው።

ያለው ሥርዓት መለወጥ አለበት። ይህ ለውጥ የሚመጣው ደግሞ ፤ በሕዝባዊ አመፅ ብቻ ነው ። በአሁኑ ወቅት ሁኔታዎች ሁሉ የሚጠቁሙት ፤ የሕዝባዊው አመፅ በየቦታው እያቆጠቆጠ መምጣቱን ነው ። " **ጀልባዋ መስጠም ስትጀምር፤ ብልህ አይጦች ከጀልባዋ ለመውጣት ይሽቀዳደማሉ።** " እንደሚባለው፤ በአሁኑ ወቅት፤ የወያኔ ባለሥልጣናትና ካድሬዎቻቸው፤ የጸጥታ ሃላፊዎችና ሰላዮቻቸው፤ አባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው በብዛት ሀገር እየለቀቁ በመሸሸ ላይ ይገኛሉ **።የሮጠ አመለጠኝ የበላ ቀደመኝ !** በማለት፤ እስካሁን ያሸሹትን ሀብት በሠላም ለመብላት በመሽቀዳደም ላይ ናቸው። በዚህ ሣምንት ብቻ ቁልፍ ቁልፍ የመረጃ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ወደ ምዕራቡ ዓለም ኮብልለዋል ። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው፤ ዘረኛው አገዛዝ ከመጨረሻው የመሰናበቻው ጊዜ መድረሱን ነው ።

የተነቃነቀን ጥርስ ለማስወገድ ግን ጠንካራ ቡጢ/ ምት ያስፈልገዋል ። ያ ጠንካራ ምት ደግሞ፤ ኃይለኛው ሕዝባዊ አመፅ ብቻ ይሆናል ።

ይህን ዕውን ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም-ተከተል መፈጸም ያስፈልጋል ።

1ኛ . የሁሉም መተባበር አጣዳፊና የቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን ይገባል። ያለ ሁሉም ትብብር ወያኔን ማስወገድ አይቻልም ።

2ኛ. ሁሉንም የሚያስተባብር አንድ ታልቅ የጋራ ጉዳይ አለ። ይኸውም የጋራ ሀገርን በጋራ ለመጠቅም የኅብረት ትግል ወሳኝ መሆኑ ነው ።

3ኛ. በቂና -አምራቂ ዝግጅት ወሳኝ ነው ። ሕዝብ ሳይዘጋጅ በመቅረቱ ካሁን በፊት፤ ሁለት ዕድሎቹን የጦር መሣሪያ በያዙ ነጣቂዎች ተወስደውበታል ። ሦስተኛ ሊነጠቅ አይገባውም ። የዛሬው አባባል ፤ ሠርገኛ መጣ ቃሪያ ቀንጥሱ፤ ሳይሆን፤ **ሠርገኛ መጣ ቃሪያ ትከሉ!** ሆኗል። ይህም የሚያመለክተው ምንም ያኅል ገና ዝግጅት አንዳልተደረገ መሆኑን የሚገልፅ ነው ። የዝግጅት ጠቋሚ ነው ።

4ኛ. መዳህኒቱ ያለው ያው፤ ከራሳችን ከኢትዮጵያውን እንጅ ከየትም፤ ከማንም እንዳልሆነ መረዳ ይኖርብናል። ለችግሩም ሆነ ለመፍትሄ፤ ሌላ ምክንያት መፈለግ አይረዳንም ። ሴትዮዋም ይህንን ተረድታ ይመስላል፡-

**" በገብስማ ዶሮ እየተመካኘ**

**የኔማ መድኅኒት ሰው ሆኖ ተገኘ ። "** ብላ ያቀነቀነችው ።

በመሆኑም፤ ሀገራችንን ለማጥፋትም ሆነ ለማዳን የመጀመሪያዎቹ ተጠያቂዎች እኛው ራሳችን መሆናችንን አምነን መተባበር አለብን።

ባለፈው ሣምንት ካርቱም ላይ የተደረገውን የዐባይ ውል ኢትዮጵያ አምርራ ትቃወመዋለች!

የሀገራችን ሉዓላዊነት በትግላችን ይከባራል!

ኢትዮጵያም ለዘለዓለም ትኖራለች !